# ህዝብና መንግስት በኤርትራ ጉዳይ ላይ

አስራት አብርሃም

*"ከእንግዲህ እጄን አጣጥፌ አልቀመጥም፤ በኤርትራ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ እወስዳለሁ።"*
የኢትዮጵያ መንግስት

*"እቲ ናይ መጀመሪያ እንኳ ኣድጊይ ኣፐፉኡላይ!"*
የትግርኛ ተረት

ያው እንደተለመደው ይሄኛው ርዕሰ ጉዳያችንም በወግ ብንጀምረው አይከፋም። ከላይ ያለው የትግርኛ ተረት የተተረተበትን አውድ ለዛሬው ወጋችን እንደማጣፈጫ እንጠቀምበታለን። ታሪኩ እንዲህ ነው፤

ከኮረዳ ጋር ሲላፉ አህያ የጠፋበት እረኛ ከሩቅ ሆኖ ኮረዳዋን ይጣራና "አህያ አላየሽም ወይ" ይላታል።

ያለውን በትክክል ያልሰማችው ልጅት "እንደቅድሙ ነይ እንጫወት" ነው ያልከው? ብትለው፤ በአነጋገሯ ተናዶ "ፊተኛውንም አህያዬን አስጠፍቶብኛል" አላት ይባላል።

የኢህአዴግ መንግስትም ፊተኛውን ጦርነት በአግባቡ መምራት ተስኖት በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የአገሪቱን ዜጎች አስጨርሶ ሲያበቃ በመስዋዕትነት የተገኘውን ድል በስምምነትና በፍርድ ቤት ስም መልሶ ካስረከበ በኋላ ኑ! ደግመን እንዋጋ እያለን ነው። ኢህአዴግ ለህዝቡ ያለው ንቀት ምን ያህል እንደሆነ ለመረዳት ከዚህ በላይ ማስረጃ ማግኘት አይቻለም። ህዝባችን በሉአላዊነቱ እንደማይደራደር ስለሚያውቁ "ሉአላዊነታችን ተደፈረ" በማለት የራሱን የስልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ፣ የህዝቡን የኑሮ ውድነት ምሬት ማደንዘዣ፣ የሊዙን አዋጅ ማስረሻና በህዝቡ ውስጥ ያለውን የለውጥ ፍላጎት አቅጣጫ ማስቀየሻ ይሆነው ዘንድ ይዋጋም አይዋጋም የጦርነት ዜማ፣ የእዋጋለሁ ቀረርቶ እያሰማ ነው የሚገኘው። ይህም "ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል በኤርትራ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ትገደዳለች" የሚል የማታሊያ ሽፋን ተሰጥቶት በፕሮፖጋንዳ መልክ ወደ ህዝቡ እየተረጨ ነው። ለመሆኑ ኢትዮጵያ ናት ወይስ አቶ መለስ ናቸው ስልጣናቸው ለመከላከል እንድንዘምት እየፈለጉ ያሉት?! ለመሆኑ ኢትዮጵያ ምን የቀረ ነገር ኖራት ነው ራሷን ለመከላከል ወደ ጦርነት የምትገባው?! ግዛቶቿና የባህር በሯ ድሮ በነፃ አስረክባ የለ! *"ተራ ህዝብ ማለት እንደዚህ በጥቂቱ የሚያምኑት የዋህ መንጋ ነው። ለፖለቲካው ሸንገላ ተዘጋጅቶ የሚጠብቅ!"* አለ ስብሀት ገብረ እግዚአብሄር። ኢህአዴግ ለህዝቡ ያለው አመለካከት ከዚሁ ፍልስፍና ብዙም የሚርቅ አይደለም።

እኛ(እኛ ስል ተራው ህዝብ ማለቴ ነው) ደግሞ እንላለን! ከአሁን በኋላ ወንድማችን ከሆነው የኤርትራ ህዝብ ጋር ጦርነት ማድረግ አያስፈልገንም። ያለብን ያለመግባባትና የይገባኛል ጥያቄም ቢሆን ለወደፊት ሁለቱም ህዝቦች የሚወክሉ በህዝቡ ይሁንታ ብቻ የተመረጡ፣ ዴሞክራሲያዊ መንግስታት በሁለቱም አገሮች ሲቆሙ ያን ጊዜ በሰላማዊ መንገድ በድርድር የሚፈታ ነው የሚሆነው። በሁሉም ወገን ቀናነት ካለ ምንም ዓይነት የማይፈታ ችግር ሊኖር አይችልም።

በመሰረቱ ለእኔ ከኢትዮጵያ ሉአላዊነት አንፃር ኢህአዴግና ሻዕቢያ ምንም የተለየ አቋም ያላቸው አይደሉም። ለኢትዮጵያ ህዝብ ቁልፍ የሆነው የወደብ ባለቤትነት ጉዳይ ላይ ኢህአዴግ ያለው አቋም ሁላችንም የምናውቀው ነው። ሻዕቢያም ሆነ ኢህአዴግ ሁለቱም "አሰብ የኤርትራ እንጂ የኢትዮጵያ መሆን የለበትም" በሚለው አቋማቸው በጣም የሚመሳሰሉ ናቸው። ስለዚህ ሁለቱም አምባገነን መንግስታት ለራሳቸው ድብቅ አጀንዳ ሲሉ ወንድማማች የሆነውን ህዝብ ዓላማ በሌለው ጦርነት በመማገድ ዘላቂ የሆነ ጠላትነት እንዲፈጠር የሚያደርገው የሁለቱም ሻዕቢያዎች ጦርነት ማድመቂያ መሆን የለብንም።

ነገር ግን የኢህአዴግ መንግስት ጦርነት ካልገጠምኩ ሞቼ እገኛለሁ የሚል ከሆነ "በደህና ከተመለሱ እንበላለን፣ ከሞቱም እንስማለን" እንዳለችው የነጋዴ ሚስት ዓይነት አቋም ሊኖረን አይችልም። ምክንያቱም አንድም አቶ መለስም ሆነ አቶ በረከት እዚህ በምኒልክ ቤተመንግስት ቁጭ ብለው (የራሳቸውን ልጆች ውጭ ልከው እያስተማሩ) የድሀውን ልጅ ይማግዳሉ እንጂ ራሳቸው አይዘምቱም። አቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ እንኳ መቼውም ቢሆን ሊዘምቱ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ አይደሉም!

ስለዚህ ኢህአዴግ ህዝቡ ከጎኑ እንዲሰለፍለት ከፈለገ በመጀመሪያ በአገር ሉአላዊነት ላይ ያለው አቋም ማስተካከል፣ ከአሁን በፊት የፈፀማቸውን ስህተቶችን መረምና በዚህ ምክንያት በአገር ላይ ለደረሰው ጥፋት ደግሞ ህዝቡን ይቅርታ መጠየቅ መቻል አለበት። ከዚያ ቀጥሎ ከህዝቡ ፍላጎት ጋር የሚሄዱ፣ የጋራ መግባባት እንዲፈጠር የሚያደርጉ አዎንታዊ እርምጃዎችን መውሰድ መቻል ይኖርበታል። ይህም፤

1 የአልጀርሱን ስምምነት መሰረዝ

የአልጀርሱን ስምምነት ለመሰረዝ የሚያስችሉ ከበቂ በላይ የሆነ ምክንያት አለን።

አንደኛ የኤርትራ መንግስት ለሰላም ቀጠናነት የተከለለውን አከባቢ አፍርሶ ወታደሮቹን ያሰፈረበት በመሆኑ፤

ሁለተኛ በአካባቢው ላይ ሰላም ለማስፈን ተሎ ሰፍሮ የነበረውን የተባበሩት መንግሰታት ጦር ስራ በማደናቀፍና በመስተጓጎል ከአከባቢው ለቆ እንዲወጣ ምክንያት በመሆኑ፤

ሶስተኛ የአልጀርሱን ስምምነት አላማ በሁለቱንም አገሮች መሀል ሰላም ለማውረድና የጠላትነትን መንፈስ ለማስወገድ ተብሎ የተደረገ ቢሆንም የኤርትራ መንግስት ከስምምነቱ በኋላም ኢትዮጵያን በማወክና ሰላምዋን በማደፍረስ ተግባሩ የቀጠለበት በመሆኑ፤

ከዚያም አልፎ የኢትዮጵያን ሰላምና መረጋጋት የሚያውኩ ኃይሎችና አሸባሪዎችን ጥላ ከላላ በመሰጠት፣ በማስታጠቅና በማስልጠን በአገሪቱ ውስጥ የተረጋጋ ሁኔታ እንዳይኖር እያደረገ በመሆኑ፣ እና ሌሎችም ምክንያቶች በማስቀመጥ የአልጀርሱን ስምምነት በአስተማማኝ ሁኔታ መሰረዝ ይቻላል። የአልጀርሱን ስምምነት ከተሰረዘ ደግሞ የሄጉ የፍርድ ቤት ውሳኔም አብሮ የሚሻር ነው የሚሆነው። ምክንያቱም የሄጉ የግልግል ፍርድ ቤት የቆመው በአልጀርሱ ስምምነት መሰረት ስለሆነ ስምምነቱ ከፈረሰ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ራሱን ችሎ ሊቆም ስለማይችል ነው።

የአልጀርሱን ስምምነት እንዲዘረስ ከሚያስፈልግበት ዋናው ምክንያት ለኢትዮጵያ ተገቢ ያልሆኑና በአዋጅ የሻረቻቸውን የቅኝ ግዛት ውሎች ተመስርቶ የኢትዮ ኤርትራን ድንበር መካለል አለበት የሚል በመሆኑና ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ከተፈጥሯዊው የባህር በሯ ውጭ የሚያደርጋት፣ ድሮ በጠላቶቿ የተዘጋጀላትን ወጥመድ ውስጥ የሚከታት በመሆኑ ነው።

## 2 የባህር በራችን የማስመላስ ጥያቄ አግባብነት መቀበል

ኢህአዴግ ስልጣኑን ለማደላደል ሲልና በሌላም ያልታወቀ ምክንያት በተፈፀመው ታሪካዊ ስህተት ምክንያት የባህር በራችን እንዳጣን የብዙ ኢትዮጵያዊያን እምነት ነው። በመሆኑም ከዚያ ወቅት ጀምሮ ኢትዮጵዊ ሁሉ ያለአግባብ የተነጠቀው የባህር በሩን የሚመለስበት ቀን በተስፋ በመጠበቅ ላይ ነው የሚገኘው። ባገኘው አገጣሚ ሁሉም አጀንዳው ከማንሳት ወደኋላ ያለበት ጊዜ የለም። ይህን ሀቅ ከመገንዘብ ይመስላል በኢትዮጵያ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳዩን በዋና አጀንዳነት በመያዝ ከኢህአዴግ ጋር ያላቸውን መሰረታዊ ልዩነት እንደ አንድ ማሳያ አድርገው ሲጠቀሙት የምናየው።

በአገሪቱ ያሉት ታዋቂ የሕግና የታሪክ ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ በህጋዊ፣ ሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ መንገድ ተጠቅሞ የኢትዮጵያ ተፈጥሯራዊ የሆነው የባህር በሯ ማስመለስ እንደሚቻል ነው። ለዚህ እውን መሆን በአሁኑ ሰዓት ብቸኛ እንቅፋት ሆኖ የሚገኘው በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ብቻ ነው። ስለዚህ ኢህአዴግ ከኤርትራ ጋር ጦርነት ለማድረግ ከመነሳቱ በፊት ይህን ሀቅ መቀበልና ለተግባራዊነቱ ቆርጦ መነሳት ሊኖርበት ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ በኩል የሚኖረው ጫና እንዴት መቀነስና ማቀዝቀዝ እንደሚቻልም ቀድሞ መዘጋጀትና መስራት የሚያስፈልገው ነው የሚሆነው።

## 3 የአመራር ለውጥ ማድረግ

በሕገመንግስቱ አንቀፅ 74 ንዑስ ቁጥር አንድ መሰረት “የአገሪቱ ጠቅላይ ሚንስትር የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ነው” ይላል። በአሁኑ ጊዜ የአገሪቱን ጠቅላይ ሚንስትር ሆነው እየሰሩት ያሉት አቶ መለስ ዜናዊ ደግሞ ካላቸው ግላዊ አመለካከት የተነሳ ከኤርትራ ጋር የሚደረግን ጦርነት ለመምራት የሚያስችል የሞራል ብቃት ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም። ከአሁን በፊትም ከኤርትራ ጋር በተደረገው ጦርነት ተገቢ አመራር መስጠት ያለመቻላቸው አንድ ነገር ሆኖ ጦርነቱ ውጤት እንዳይኖው፣ የኤርትራ መንግስት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በእነስዬ ሊደመሰስ በተቃረበበት ሰዓት ጥላና ከላላ ሆነው እንዳዳኑት ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። በዚህ ምክንያት ነው የኤርትራ መንግስት እስከዛሬም ድረስ ዋነኛ ስጋት ሆኖ እንዲቀጥል ያደረገው። ያኔ የኤርትራ መንግስት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተደምስሶ ቢሆን ኖሮ የአሁኑ የጦርነት ነጋሪትም ባልተሰማ ነበር።

ስለዚ ኢህአዴግ ከኤርትራ ጋር ጦርነት ለማድረግ ቁርጠኛ ሃሳብ ካለው በመጀመሪያ ጠቅላይ ሚንስትሩን መቀየር መቻል አለበት። እውነት ለአገሩ የሚቆረቆርና በራሱ ሳንባ የሚተነፍስ የኢህአዴግ አመራር (የፓርላማ አባል) ካለ በቅድሚያ ማድረግ ያለበት ይህንኑ ነው። ለአዳዲሶቹ የኢህአዴግ አባላት ይህ ሀሳብ እንግዳ ነገር እንዳይመስላቸው ከአሁን በፊትም ኤርትራ በወረረችን ጊዜ ይህ ጥያቄ ራሱ በኢህአዴግ ውስጥ ተነስቶ እንደነበር ላስታውሳቸው እፈልጋለሁ።

ነገሩ እንደዚህ ነው። የኤርትራ ወረራ እንደተሰማ “ምን ብናደርግ ይሻላል?” ብለው በመጀመሪያ የህወሀት የሥራ አስፈፃሚ አባላት ስብሰባ ይቀመጣሉ። በዚህ ጊዜ ወረራውን በኃይል መመከት አለብን የሚለው የአብዛኛው ተስብሰቢ አቋም የነበረ ቢሆንም አቶ መለስ

“ወረራውን በኃይል መመከት የለብንም። የኤርትራ መንግስት አሁን ከያዘው በላይ እንዳይሄድ እየተከላከልን የልማት ስራችንን እንቀጥል” ዓይነት ሀሳብ ያቀርባሉ። ነገርዬው ጄኔራል አማን አንዶም በደርጉ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ አቅርበውት ነበር እየተባለ ከሚነገረው የአንድ ወገን ብቻ የጦርነት ማቆም ሀሳብ ጋር የሚመሳሰል ነው።

በዚህ የአቶ መለስ አቋም የተበሳጩት አንድ የአመራር አባል ማንም ከዚያ በፊት አስቦት የማያውቀው ጥያቄ አነሱ። “እንግዲያውስ በኃይል የተደፈረውን ሉአላዊታችን በኃይል የማስመለስ ጉዳይ  የማታምንበት ከሆነ ይህን አቋም ይዘህ ጦሩን በበላይነት ልትመራ ስለማትችል ከስልጣንህ ውረድ” ይላሉ። አቶ መለስ የበጋ መብረቅ የመታቸው ያህል ነው የሆኑት ይላሉ በወቅቱ በዚያ የነበሩት ሰዎች ሲናገሩ።

እንዲያም ሆኖ እንደምንም ብለው ስሜታቸውን ተቆጣጥረው መጀመሪያ  ከነበራቸው አቋም ለስለስ ያለ አቀራረብ ይዘው በእርጋታ መናገር ጀመሩ። “ውረድ ከእንግዲህ አንፈልግህም” ያላቸውን ጓድ ከልጅነት ጀምሮ እንደሚያውቁና እንደሚያደንቁትም ጭምር በመግለፅ ሁለቱ ብቻ የሚያውቋቸው ሚስጥሮች እንደነበራቸው በወግ መልክ በማቅረብ (ምንም እንኳ የሁለታችን ሚስጥሮች ነበሩ ብለው ያቀረቧቸው ነገሮች ከስብሰባውና ከተነሳው አጀንዳ ጋር ምንም ተያያዥነት ባይኖራቸውም ሰውዬው “ምነው ይህን ጥያቄ ባላነሳሁት!” የሚል ስሜት እንዲያድርበትና በጥያቄ እንዳይገፊበት የሚያደርግ የውስጠ ልመና ዓይነት ነበር) በስብሰባው ውስጥ ተፈጥሮ የነበረውን ክውታ (ቀጥሎ ምን ይሆናል የሚል ድንጋጤ) ወደ ሳቅ ለወጡት። የተሰብሳቢው ቀልብ በደንብ ወደ እርሳቸው እንዳጋደለ ካረጋገጡ በኋላ “እኔ ከወረድኩ ማን ጠቅላይ ሚንስትር እንደሚሆን አስባቹበታል?!” ዓይነት ቅላፄ ያለው ንግግር አደረጉ። የእርሳቸው የቁርጥ ቀን ደጋፊዎች የሚባሉት ደግሞ አጋጣሚውን በመጠቀም ተጨማሪ ማጠናከሪያ በመስጠት “ብፃይ መለስ ችግር ብኖርበትም የእኛው ነው። የቁርጥ ቀን ጓዳችን ነው። እኛው እዚሁ እናርመዋለን እንጂ እንዴት ለሌላ አሳልፈን እንሰጠዋለን። በማለት ነገርዬው በዚያው እንዲዘጋ አደረጉት። መለስ በሌላ የመተካቱ ሃሳብ ያነሱትም በደንብ የተዘጋጁበት ጉዳይ ስላልነበረ፣ ስለሚተካው ሰውም እርግጠኞች ስላልነበሩ “ከማያውቁት መልዓክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል” ብለው ዝም አሉ። (መለስን ከስልጣን የማውረዱ ሀሳብ ግን ከዚያች ቀን ጀምሮ በኋላ አንጃ ተብሎ “ስብሰባን ረግጦ በመሄድ” ወንጀል ስም የተባረረው ቡድን የሚመደቡ አንዳንድ አመራሮች አእምሮ ውስጥ እንደተፀነች የሚገምቱ አሉ)

ያም ሆነ ይህ አቶ መለስም አንድ ቀን ሊተኩ እንደሚችሉ፣ የሚተኩ ከሆነ ደግሞ ቀጥሎ የሚኖረው አመራር ምን እንደሚመስል በዓይነ ልቦናቸው እየታያቸው ለጊዜው ጉዳዩ በዚሁ ዘግተው ወደ ቀጣዩ የኢህአዴግ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ያመራሉ። እዚያም ወረራውን በኃይል የመቀልበሱ ጉዳይ አቶ መለስ ተቃውመውታል ሲባል በአዳራሹ ውስጥ ትልቅ አቧራ አስነሳ። ከብአዴን አመራር ውስጥ አንዱ ተነስቶ “እንግዲያውስ በዚሁ ሁኔታ ላይ ሆነን ጦርነት ገጥመን ማሸነፍ ስለማንችል ሌላ መሪ መቀየር አለብን” ይላል። ይሄው የተፈራው ነገር ደረሰ የሚል ስሜት በህወሀት ሰዎች ዘንድ በመፈጠሩ ቅድም ይውረድ ብለው ሲከራከሩ የነበሩት ሳይቀሩ ሀሳቡን ክፉኛ ተቃወሙት። አሁን ጠቅላይ ሚስተር ብንቀይር ለጠላት ውስጣዊ ያለመረጋጋት ሁኔታ እንዳለን የሚያመላክት ነው የሚሆነው። ለህዝቡም፣ ለጦሩም ተመሳሳይ መልዕክት ነው የሚያስተላልፈው ከዚህ ይልቅ ጦሩ በጠቅላይ ሚንስትሩ ሳይሆን በኮሚቴ (በኋላ ኮማንድ ፖስት የተባለው ማለት ነው) እንዲመራ ማድረግ እንችላለን ብለው ተረባርበው አቶ መለስን ከመውረድ አተረፏቸው። ብአዴኖችም በዚሁ አጋጣሚ ወደ ዋናው ስልጣን ለመምጣት ያደረጉት የመጀመሪያው ሙከራቸው ለጊዜው ሳይሳካላቸው ቀረ(ሁለተኛው የህወሀትን ክፍፍል ተንተርሰው ከመለስ ጎን በመቆም ያካሄዱት ነው። እሱም አልሆነላቸውም። አቶ መለስም አስቸጋሪውን ጊዜ ከብአዴኖች ጋር ሆነው ካሳለፉት በኋላ አቶ በረከትን አስቀርተው ሌሎቹን ከስልጣን ትግሉ ውጪ አደረጓቸው። እንዲህ ያለውን ነገር “መኮረኒን በግል መከራን በጋራ” ይሉታል -ዶ/ር መረራ ጉዲና! ለነገሩ ብአዴኖች አቶ ታምራት ላይኔ እንዲታሰሩ ሲወስኑ ነው ነገሩ የተበላሸባቸው)

ይህን ታሪክ በሰፊው ያመጣሁት በኢህአዴግ ውስጥ “ጠቅላይ ሚንስትሩ ይነሱ” የሚለው ሀሳብ አዲስ አይደለም ለማለት ነው። በህወሀት ውስጥም ቢሆን ይህን ጉዳይ ማንሳት ወሳኝ ነው የሚሆነው። በጦርነት ቀጠና ውስጥ ገብቶ በጭንቀት ለሚኖረው የትግራይ ህዝብ ነው በቅድሚያ ማሰብ ያለባቸው። አቶ መለስ በኤርትራ ላይ ያላቸውን አቋም ትክክል እንዳልሆነ የሚሰማቸው የህወሀት አባላት እንዳሉ የሚታወቅ ነገር ነው። ችግሩ ግን ከእኔ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ መገደል በኋላ የነበሩት የደርግ አመራርና ከህወሀት ክፍፍል በኋላ ያላሁት የህወሀት አመራሮች አንድ የመሆናቸው ጉዳይ ነው። ሁለቱም የሲ.ቃነመናብርቱ ፍጠራን ናቸው። ስለዚህ በፈጣሪያቸው ላይ ይነሳሉ ተብሎ አይጠበቅም።

## 5 ብሄራዊ መግባባት መፍጠር

ኢህአዴግ በአገር ውስጥ ያሉትም ይሁን በውጭ ያሉት እውነተኛ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ለአገር ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ሳያስቀምጥ መደራደር መቻል አለበት። በሂደትም ብሄራዊ መግባባት እንዲፈጠር፣ ከእነዚህ ኃይሎች ጋር ሆኖ ለመስራት መወሰንና ለተግባራዊነቱ  ደሞ መንቀሳቀስ ይኖርበታል።

እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ሳያፈፅሙ ወደጦርነት አመራለሁ ማለት የሚያስከትለውን ጦስ በቅጡ አለመገመት ነው የሚሆነው። ህዝቡ እንደበፊቱ ድጋፉን ይሰጠኛል፤ ሰራዊቱም ጠንክሮ ሊዋጋ ይችላል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው የሚሆነው።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

(ፍትሕ ጋዜጣ፥ ጥር 25/2004 ዓ.ም)

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
Febuary 3, 3012